የኢትዮጵያ
ሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ (ኢሰመጉ)

# 7ኛ ሀገራዊ ምርጫ አጠቃላይ ሪፖርት




ነሃሴ 2018 ዓ.ም

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

**ዋና ጽ/ቤት፡ አዲስአበባ**

**አ.አ ስታዲየም አጠገብ፣ላሊበላ ሬስቶራንት ጎን፣ ሣኅለ ሥላሴ ሕንፃ 8ኛ ፎቅ፣ቢሮ ቁጥር 19**

**ኢ-ሜይል:info@ehrco.org**

**ድረገጽ: www.ehrco.org**

**ፌስቡክ፡https://www.facebook.com/ehrco1/**

**ትዊተር፡ https://www.twitter.com/ehrcoethio**

**ቴሌግራም፡ https://t.me/ehrco**

**የፖስታ ሳጥን ቁጥር 2432**

**አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ**

**የሰብዓዊ መብቶች ክትትል እና ምርመራ መምሪያ፡ አዲስ አበባ**

**ስልክ: (+251) 011 558-2387**

**ኢሜይል:info@ehrco.org**

**ቀጠና / ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች**

**ደቡብ ኢትዮጵያ ቀጠና፡**

**ሐዋሳ - ስ.ቁ (+251) 046 220-4500፣ ፖ.ሳ.ቁ 360**

**አርባምንጭ ስ.ቁ (+251)0461818344**

**ሰሜን ኢትዮጵያ ቀጠና፡ባሕርዳር- ስ.ቁ (+251) 058 220-0240፣ ፖ.ሳ.ቁ 1115**

**ምሥራቅ ኢትዮጵያ ቀጠና ሐረር - ስ.ቁ (+251) 025 411 6845፣ ፖ.ሳ.ቁ 2596**

**ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ቀጠና፡አዲስ አበባ- ስ.ቁ (+251)011 551-7704፣ ፖ.ሳ.ቁ**

## Contents


ምስጋና.....5

1. አጭር ዳሰሳ፣.....6
2. ኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ (ኢሰመጉ) .....7
3. መግቢያ.....9
4. የኢሰመጉ የምርጫ ሥራዎች.....10
5. የምርጫ መታዘብ ዋና አላማ.....11
6. የምርጫ ስራው ወሰን.....12
7. የምርጫ ትዝብት ስነ-ዘዴ (Observation Methodology) .....12
8. ያጋጠሙ ተግዳሮቶች እና የአሰራር ገደቦች.....13
9. ከምርጫ ጋር የተያያዙ የህግ ድንጋጌዎች .....13
10. ቅድመ ምርጫ ክትትል (Pre-Election monitoring).....15
    - 10.1. የመራጮች ምዝገባ.....15
    - 10.2. የምርጫ ታዛቢዎች ምልመላ.....15
    - 10.3. የምርጫ ትምህርት .....16
    - 10.4. የዕጩዎች ምዝገባ.....19
    - 10.5. የፖለቲካ ፓርቲዎች ዝግጅት እና የምርጫ ቅስቀሳ .....20
    - 10.6. የሚዲያ ሽፋን.....20
    - 10.7. የሴቶች፣ የወጣቶች እና የአካል ጉዳተኞች ተሳትፎ .....21
11. የምርጫ ቀን ምልከታ (Election Day Observation) .....22
    - 11.1. የምርጫ ጣቢያዎች መከፈት.....22
    - 11.2. የድምፅ አሰጣጥ ሚስጢራዊነት በተመለከተ- .....22
    - 11.3. የፓርቲ ወኪሎችና ታዛቢዎች መገኘት፤ .....22
    - 11.4. ጸጥታና ደህንነት .....23
    - 11.5. በምርጫ ዕለት ግኝቶች.....23
    - 11.6. የምርጫ ጣቢያዎች መዘጋት እና ቆጠራ .....24
12. የውጤት አስተዳደር (Results Management) .....25
13. የሰብአዊ መብቶች ግምገማ (Human Rights Assessment).....26

14. ዋና ዋና ግኝቶች (Key Findings) ....................26
14.1. አዎንታዊ ምልከታዎች ....................26
14.2. ተግዳሮቶች/ያጋጠሙ ችግሮች....................27
➢ ዲጅታል የምዝገባ ....................27
15. ምክረ-ሃሳቦች (Recommendations) ....................28

# ምስጋና

ኢሰመጉ ከምርጫ ጋር የተያያዙ ስራዎችን ለመስራት  የጀት  እጥረት ገጥሞት የነበረ ቢሆንም ለምርጫው የተወሰነ ጊዜ ሲቀር ከ United Nations Development Program (UNDP) እና European Centre for Electoral Support (ECES) በተገኘ ገንዘብ የመራጮች ትምህት፣ በምርጫው ሂደት የምርጫ ትዝብት ስራ ሰርቷል። Civil Rights Defender (CRD) በተገኘ ድጋፍ የታዛቢዎች ስልጠናን መስጠት ችሏል።  በተመሳሳይ ኢሰመጉ የምርጫ ታዛቢዎችን ለማሰማራት የበጀት  እጥረት ገጥሞት የነበረ ሲሆን የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ድርጅቶች ህብረት (ኢሰመድህ)  ባደረገው ድጋፍ ኢሰመጉ ያሰለጠናቸውን የምርጫ ታዛቢዎች ማሰማራት እንዲችል አጋርነቱን አሳይቷ።

ኢሰመጉ በሁሉም የምርጫ ሂደቶች ውስጥ ድጋፍ ላደረጉ  ድርጅቶች በሙሉ ምስጋናውን ያቀርባል።

## 1. አጭር ዳሰሳ፣

የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ(ኢሰመጉ) ላለፉት 34 አመታት በተካሄዱ ጠቅላላ ምርጫዎች፣ የአካባቢ ምርጫዎች፣ የማሟያ ምርጫዎች፣ ድጋሚ ምርጫዎች እና የህዝበ ውሳኔዎች ላይ የመራጮች ትምህርትን በመስጠትና በታዛቢነት ተሳትፏል። ኢሰመጉ በትዝብት ስራው አላማ አድርጎ የተነሳው 7ኛው ሀገራዊ ምርጫ ፍትሀዊ፣ ነጻና ገለልተኛ የነበረ መሆኑን ለማረጋገጥ እና የትዝብት ግኝቱን መሰረት በማድረግ በሀገር አቀፍ ደረጃ የተካሄደ ምርጫ ላይ የታዩ ክፍተቶችን በማመላከት በቀጣይ ለሚደረጉ ምርጫዎች ማስተካከያ እንዲደረግ ምክረ ሀሳቦችን ለማቅረብ ነው።

በዚህም መሰረት ኢሰመጉ በ7ኛው ሀገራዊ ምርጫ ከምርጫ ቦርድ ባገኘው የታዛቢነት ፈቃድ መሰረት ቅድመ ምርጫ፣ የምርጫ እለት እና ድህረ ምርጫ ስራዎችን ሰርቷል። በቅድመ ምርጫ ወቅትም ዜጎች ለምርጫ ተነሳሽነት እንዲኖራቸው እና በዕውቀት ላይ የተመሠረተ ምርጫ እንዲያከናውኑ እንዲሁም ዴሞክራሲያዊ መብቶቻቸውን እንዲጠቀሙ በማሰብ ለ192 ሰዎች የአሰልጣኞች ስልጠና በመስጠት ከ 22,694 በላይ ለሆኑ ሰዎች የምርጫ ትምህርት የሰጠ ሲሆን ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ ማለትም በራሪ ወረቀቶችን በመጠቀም ከ 303,880 በላይ ዜጎች ስለ ምርጫ ግንዛቤ እንዲያገኙ ማድረግ ተችሏል። በምርጫ እለትም 433 ታዛቢዎችን መልምሎ በማሰልጠን በ6 ክልሎች ማለትም በሀረር፣ በሲዳማ፣ በሶማሌ፣ አማራ፣ በኦሮምያ እና በደቡብ ኢትዮጵያ ክልሎች እና በሁለት ከተማ መስተዳድሮች (አዲስ አበባ እና ድሬዳዋ) የምርጫ ታዛቢዎችን በማሰማራት የምርጫውን ሂደት ለመታዘብ ችሏል።

የመራጮች ምዝገባ ጋር ተያይዞ በኦሮምያ እና በአማራ ክልል የተወሰኑ አካባቢዎች እንዲሁም በትግራይ ክልል ከጸጥታ ስጋት ጋር ተያይዞ ምርጫ ሳይካሄድ ቀርቷል። ይህም ዜጎች ዴሞክራሲያዊ መብታቸውን እንዳይጠቀሙ ተግዳሮት ሆኗል። በምርጫው ሂደት የወጣቶች፣ የአካል ጉዳተኞች እና የሴቶች በዕጩነት፣ በመራጭነት እና በምርጫ አስፈጻሚነት የነበራቸው ተሳትፎ የሚበረታታ ሲሆን ኢሰመጉ ታዛቢዎችን ባሰማራባቸው የምርጫ ጣቢያዎች ከ50% በላይ ሴቶችና ወጣቶች በምርጫ አስፈጻሚነት ተሳትፈዋል። ኢሰመጉ በታዘበባቸው አብዛኛዎቹ የምርጫ ጣቢያዎች በተያዘላቸው ሰዓት የተከፈቱ መሆኑን፣ በድምጽ አሰጣጥ ሂደቱ ሚስጢራዊነቱ የተጠበቀ መሆን የነበረበት ቢሆንም የምርጫ አስፈጻሚዎች ወደ ድምጽ መስጫ ሳጥኖች በመግባት ህዝቡ በነጻነት እንዳይመርጡ ማድረጋቸውን እና የምርጫውን ነፃና ገለልተኝነት ማስጠበቅ ይቻል ዘንድ የፓርቲ ወኪሎች እና ታዛቢዎች በምርጫ ጣቢያዎች መገኘት የነበረባቸው ቢሆንም በአንዳንድ ምርጫ ጣቢያዎች በተለይም ከከተማ ውጪ በነበሩ የምርጫ ጣቢያዎች የፓርቲ ወኪሎች እና ታዛቢዎች በምርጫ ጣቢያዎች ያልተገኙ መሆኑን ኢሰመጉ ታዝቧል።

በሌላ በኩል የምርጫ ቦርድ የምርጫ ጣቢያዎች የሚዘጉበትን ሰዓት በማራዘሙ ምክንያት እና የምርጫ ቦርድ ያደረገው የሰዓት ማራዘሚያ ግልጽነት የጎደለው እና ብዙ የምርጫ ጣቢያዎች የመዘገቧቸውን መራጮች አስመርጠው የጨረሱ ቢሆንም የቆጠራ ሂደታቸውን በመደበኛ ሰዓታቸው ማድረግ እንደሚችሉ ባወጣው መግለጫ ላይ በግልጽ ባለማስቀመጡ እና መራዘሙ የተገለጸው መደበኛው የምርጫ ሰዓት ካለቀ በኋላ በመሆኑ የጀመሩትን የድምጽ ቆጠራ ለማቋረጥ የተገደዱ መሆኑን፣ ብዛት ባላቸው የምርጫ ጣቢያዎች የቅሬታ ሰሚዎች ያልነበሩ መሆኑን፣ በዲጅታል የመራጮች ምዝገባን ማከናወን መጀመሩ መልካም ልምምድ እና ሊበረታታ የሚገባው ቢሆንም በምርጫ እለት በዲጅታል ስነስርዓት የተመዘገቡ መራጮች ምርጫ ለማከናወን ከፍተኛ ተግዳሮት ገጥሟቸው የነበረ መሆኑን እና ከዚህም ጋር ተያይዞ ሳይመርጡ የቀሩ መራጮች መኖራቸውን ኢሰመጉ ታዝቧል።

በዚህ የምርጫ ትዝብት ኢሰመጉ የምርጫ ታዛቢዎችን ካሰማራባቸው 833 የምርጫ ጣቢያዎች መካከል በ143 የምርጫ ጣቢያዎች ቅሬታ ሰሚዎች ያልነበሩ መሆኑን እንዲሁም በ 3 የምርጫ ጣቢያዎች የምርጫ አስፈጻሚዎች ለገዢው ፓርቲ ወገንተኛ የነበሩ መሆኑን ኢሰመጉ ለመታዘብ ችሏል።

ኢሰመጉ ከላይ የተገለጹትን ጨምሮ በቅድመ ምርጫ፣ በምርጫ እለት እና በድህረ ምርጫ ከታዘባቸው ትዝብቶች በመነሳት የምርጫ ቦርድ እና የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ወደፊት ለሚደረጉ ምርጫዎች የምርጫ ቅሬታ ሰሚዎች በበቂ ሁኔታ መሟላታቸውን እንዲያረጋግጡ፣ የዲጂታል የምዝገባ ስነስርዓት በበቂ ሁኔታ ማህበረሰቡ እንዲገነዘበው በማድረግ አሰራሩን እንዲያዳብሩ፣ የዜጎችን የመምረጥ መብት ከማስጠበቅ አኳያ ሰላምና ጸጥታ መደፍረስ የሚታይባቸው አካባቢዎች ወደ ሰላም የሚመለሱበትን ሁኔታ በማመቻቸት መራጮች በምርጫ የመሳተፍ መብታቸውን እንዲያስጠብቅ እና የምርጫ አስፈጻሚዎች ገለልተኝነታቸውን በተገቢው ሁኔታ ባስጠበቀ መልኩ ምልመላ እንዲያደርግ ኢሰመጉ ጥሪውን ያቀርባል።

## 2. ኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ (ኢሰመጉ)

የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ *(ኢሰመጉ)* አገር በቀል ድርጅት ሆኖ በ1984 ዓ.ም የተመሠረተና በሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ዐዋጅ ቁጥር 1113/2011 መሠረት በሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ኤጀንሲ ስር በምዝገባ ቁጥር 1146 ከ 02/11/11 ዓ.ም ጀምሮ ዳግም ተመዝግቦ በሕጋዊነት የሚንቀሳቀስ መንግሥታዊ ያልሆነ፣ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋች ድርጅት ነው።

ኢሰመጉ ለትርፍ ያልተቋቋመ፣ ነጻና ገለልተኛ፣ ከማናቸውም የፖለቲካ ፓርቲ፣ የኃይማኖት ተቋም፣ የብሔረሰብ ቡድን፣ ማኅበራዊ መደብ ወዘተ የማይወግን የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋች ተቋም ሲሆን፤ ዓላማውም በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲጎለብት፣ የሕግ የበላይነት እንዲሰፍንና የሰብዓዊ መብቶች እንዲከበሩ የበኩሉን አስተዋጽዖ ማድረግ ነው።

ኢሰመጉ እነዚህን ዓላማዎች ይዞ ላለፉት 34 ዓመታት ሁለንተናዊ፣ ሀገራዊና ሕዝባዊ ተልዕኮ በመያዝ ባከናወናቸው ተግባራት በኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች እንዲከበሩ፣ የሕግ የበላይነትና ሕጋዊ ሥርዓት እንዲሰፍን እና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲመሠረት የበኩሉን አስተዋጽዖ በማበርከት ላይ ይገኛል። ኢሰመጉ በዋነኝነት በሚታወቅበት የሰብዓዊ መብቶች አያያዝ ሁኔታን መከታተል፣ መመርመር፣ መሰነድ እና ለሕዝብ ይፋ ማውጣት ተግባሩ 40 መደበኛ መግለጫዎች፣ 157 ልዩ መግለጫዎች እና በርካታ ጋዜጣዊ መግለጫዎችን ይፋ አድርጓል። ኢሰመጉ ባለፉት ዓመታትም ሆነ አሁን በሚገኝበት አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ሆኖም ቢሆን፣ ሁኔታና ዐቅም በፈቀደለት መጠን የሰብዓዊ መብቶች መከበር፣ የሕግ የበላይነትና የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ በኢትዮጵያ እውን እንዲሆን ካለው የጸና ዓላማ አኳያ የበኩሉን ሚና እየተወጣ ይገኛል

ከቀዳሚ ሥራዎቹ መካከል በመርህ ደረጃ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓትን በጽኑ መሠረት ላይ ለማስቀመጥ እንዲያግዙ በኢትዮጵያ ውስጥ በተከናወኑ በርካታ ሀገር አቀፍ ምርጫዎች፣ አካባቢያዊ ምርጫዎች፣ ዳግም ምርጫዎች እና ሕዝበ-ውሳኔዎች ወቅት የመራጮች ትምህርት፣ የምርጫ መታዘብ እና የሰብዓዊ መብቶች ሁኔታ ክትትል ሥራዎች ላይ ንቁ ተሳትፎ ማድረግ ከዋነኞቹ ሥራዎች መካከል የሚጠቀሱ ናቸው። በእስካሁኑ ቆይታውም በአገራችን በኢትዮጵያ በተከናወኑ ልዩ ልዩ ምርጫዎች ላይ ዘርፈ ብዙ ተሣትፎዎችን አድርጓል እያደረገም ነው።

## 3. መግቢያ

ምርጫ የአንድ ዲሞክራሲያዊ ርዓት መገለጫ ባህሪ ነው ። ምርጫ ትክክለኛ የሚሆነው ደግሞ ከአንድ በላይ በምርጫ የሚሳተፉ ፓሪቲዎች ወይም ተወዳዳሪዎች ኖረው መራጩ በፈለገው አማራጭ ላይ እንዲወስን እድል የሚሰጥ ሲሆን ነው።

በዲሞክራሲ ሥርዓት የአንድ መንግስት ስልጣን የሚመነጨው ከሕዝብ ነው። ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ ምርጫ ለማካሄድ እንዲችል ይህንን ለማስፈጸም የሚችሉ ብቃት ያላቸው የምርጫ አስፈፃሚ ተቋማትና ዲሞክሪያሲዊ የሆኑ የማስፈፀሚያ ሕጎች መኖር መሰረታዊ ነው ።

የኢፌዴሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 8 (3) ላይ የህዝቦች ሉአላዊነት የሚገለፀው በዚህ ህገመንግስት መሰረት በሚመርጧቸው ተወካዮቻቸውና በቀጥታ በሚያደርጉት ዲሞክራሲያዊ ተሳትፎ አማካኝነት ይሆናል በማለት ሉአላዊ ስልጣን የህዝብ መሆኑ ተደንግጓል። አንቀፅ 38 (1) ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ በቀለም፣ በቋንቋ፣ በዘር፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ እና ሌላ አመለካከት ወይም በሌላ አቋም ላይ የተመሰረተ ልዩነት ሳይደረግበት የመምረጥ እና የመመረጥ መብት ሲደነግግ ይህን ዲሞክራሲያዊ መብቱን ነፃና ፍትሐዊ በሆነ ምርጫ አፈፃፀም ሙሉ መብቱን እንዲያስከብር በማለት የኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድን በአዋጅ ቁጥር 1133/2011 ተቋቁሟል። የምርጫ ቦርድም ከሰባተኛ ሀገርዊ ምርጫ ጋር ሰባት ሀገር አቀፍ እና የክልል ምክር ቤት ምርጫ አካሂዷል።

ሆኖም የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ (ኢሰመጉ) ምርጫው በትግራይ ክልላዊ መንግሥት ሙሉ በሙሉ፣ በተወሰኑ አማራ እና ኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥታት የሚገኙ ውስን ስፍራዎች የሚገኙ ዜጎች ድምፅ የመስጠት እድል አለማግኘታቸውን እና በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና በክልል መንግሥታት ምክር ቤቶች ውስጥ አለመወከላቸው አሳሳቢ በመሆኑ አፋጣኝ እልባት በመስጠት የማህበረሰቡ የመምረት መብት በማክበር ውክልናውን መስጠት እንዲችል ማድረግ ተገቢ ነው ብሎ ያምናል ።

የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ (ኢሰመጉ) ከምርጫ ቦርድ ያገኘውን የምርጫ ታዛቢነት እና የሥነ- ዜጋና የመራጮች ትምህርት የማስተማር ፍቃድን በመጠቀም በስድስት ክልሎች ማለትም በአማራ፣ ኦሮምያ፣ በደቡብ ኢትዮጵያ፣ በሲዳማ፣ በሐረሪ እና በሶማሌ ክልሎች እንዲሁም በአዲስ አበባና በድሬዳዋ ከተማ መስተዳድሮች በመቶዎች የሚቆጠሩ ቋሚ እና ተዘዋዋሪ ታዛቢዎችን አሰልጥኖ አሰማርቷል ። ኢሰመጉ ያሰማራቸውን ታዛቢዎች በመጠቀም የነበረውን የቅድመ ምርጫ፣ የድምፅ መስጫ ዕለት እና የድኅረ ምርጫ ሂደት ከተለያዩ መስፈርቶች አንፃር ታዝቧል። የምርጫ ታዛቢነት ሥራውን በማከናወን ረገድ ኢሰመጉ የዜጎችን ፖለቲካዊ ተሳትፎ በማሳደግ የምርጫ ሂደቱን አሳታፊነት፣ ግልጽነት፣ ተጠያቂነትና አጠቃላይ ታማኝነት ለመከታተልና ለመገምገም ጥረት አድርጓል። እንዲሁም በምርጫ ዙሪያ የአሰልጣኞች ስልጠና በመስጠት እና የተለያዩ በራሪ ወረቀቶችን በመበተን በሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎችን በመድረስ በምርጫ ዙሪያ ግንዛቤ መፍጠር ችሏል።

ይህ የምርጫ ሪፖርት ሰኔ 24/2018 ዓ.ም የተካሄደው 7ኛ ሀገር አቀፍ ምርጫ የምርጫ መመዘኛዎችን ባሟላ መልኩ ስለመካሄዱ ወይንም አለመካሄዱ ማወቅ ለሚፈልጉና ለሚገባቸው ዜጎች፣ ተቋማትና ለሌሎች ይህ ሪፖርት ተገቢዉን መረጃ ይሰጣል ተብሎ ይታመናል፡፡

## 4. የኢሰመጉ የምርጫ ሥራዎች

ኢሰመጉ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ በበርካታ ምርጫዎች ላይ ተሳትፎ ያደረገ ሲሆን፤ በዚህም በምርጫ ሥራዎች ላይ ከፍተኛ ልምድ ካካበቱ እና ተዓማኒ ከሆኑ አገር በቀል የሲቪክ ማኅበራት ድርጅቶች መካከል ቀዳሚው ነው፡፡ በልዩ ልዩ ሥራዎች ተሳትፎ ያደረገባቸውን ምርጫዎች ለመጥቀስ ያህል የሚከተሉት ይገኙበታል፡፡

- በ1992 ዓ.ም ግንቦት ወር ላይ በአገር አቀፍ ደረጃ በተካሄደው ጠቅላላ ምርጫ ወቅት የቅድመ ምርጫ ክትትል መግለጫዎችን ይፋ በማድረግ እና 109 ገለልተኛ ታዛቢዎችን አሰልጥኖ በማሠማራት በታዛቢነት ተሳትፎ አድርጓል፡፡
- ሰኔ 18 ቀን 1992 ዓ.ም በደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል በተደረገው ድጋሚ ምርጫ ወቅት 21 ገለልተኛ ታዛቢዎችን አሰልጥኖ በማሠማራት በታዚቢነት ተሳትፎ አድርጓል፡፡
- በ1993 ዓ.ም የካቲት ወር ላይ በተካሄደው የወረዳና የቀበሌ ተወካዮች ምርጫ ወቅት 550 ገለልተኛ ታዛቢዎችን አሰልጥኖ በማሠማራት በታዛቢነት ተሳትፎ አድርጓል፡፡
- ታህሳስ 14 እና 21 ቀን 1994 ዓ.ም በደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል በተደረገው የዞን፣ የወረዳና የቀበሌ ተወካዮች ምርጫ ወቅት 226 በከተማ፣ 37 በገጠር በጠቅላላ 263 ገለልተኛ ታዛቢዎችን አሰልጥኖ በማሠማራት በታዛቢነት ተሳትፎ አድርጓል፡፡
- በጥር ወር 1997 ዓ.ም በሶማሌ ክልል በተካሄደው የወረዳ ምክር ቤት አባላት ምርጫ 21 ገለልተኛ ታዛቢዎችን አሰልጥኖ በማሠማራት በታዛቢነት ተሳትፎ አድርጓል፡፡
- በ1997 ዓ.ም ግንቦት ወር ላይ በተካሄደው ጠቅላላ ምርጫ ወቅት በስድስት ክልሎችና ሁለት ከተማ መስደዳድሮች ውስጥ በመራጮች ትምህርት ስልጠና፣ በምርጫ መታዘብ እና በምርጫ ወቅት በሚፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ክትትል ሥራዎች ላይ በወቅቱ ከነበሩ የሲቪክ ማኅበራት በላይ እጅግ ከፍተኛ ቁጥር አሰልጣኞችን፣ ታዛቢዎችን እና የሰብዓዊ መብቶች ባለሙያዎችን በማሠማራት ከፍተኛ ተሳትፎ አድርጓል፡፡
- በ1997 ዓ.ም በተከናወነው አገር አቀፍ ምርጫ ወቅት ገጽ ለገጽ የመራጮች ትምህርት 125 አሰልጣኞችን አሠማርቶ በ195 የምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ በሰጠው ትምህርት ከ 400,000 ሺህ በላይ መራጮችን ተደራሽ ለማድረግ ችሏል፡፡ በቴሌቪዥንና በጋዜጣም የተሰጠው የመራጮች ትምህርት በወቅቱ ለመምረጥ ከሚችለው ከ32 ሚሊየን መካከል ሕዝብ ውስጥ አብዛኛውን ተደራሽ ማድረግ የቻለ ነበር፡፡

- በጥር 29/2015 ዓ.ም በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ክልል የ 6 ዞኖች እና የ5 ልዩ ወረዳዎች ህዝበ ውሳኔ ላይ ታዛቢዎችን በማሰማራት ተሳትፏል።

የምርጫ መታዘብን በሚመለከት በወቅቱ 1500 ያህል ታዚቢዎችን በአብዛኛው የምርጫ ጣቢያዎች በማሠማራት እጅግ ከፍተኛ የሚባል ተሳትፎ ለማድረግ ችሏል። ከእነዚህ ሥራዎች ጎን ለጎን በምርጫ ሂደቱ ወቅት የሚስተዋሉ ችግሮች እርማት እንዲሰጣቸው፣ የሰብዓዊ መብቶች እንዲከበሩ እና ሂደቱ ነጻ፣ ፍትሓዊ እና ሰላማዊ እንዲሆን ልዩ የሰብዓዊ መብቶች ሁኔታ መግለጫዎችን እና ጋዜጣዊ መግለጫዎችን ይፋ በማድረግ ከፍተኛ ተሳትፎ አድርጓል። ሕዝባዊ የውይይት መድረኮችንም በአምስት ትላልቅ ከተሞች በማዘጋጀት የምርጫ ሂደቱ ሰላማዊ እንዲሆን ለማድረግ ጥሯል።

ከምርጫ 97 ማግስት በተፈጠሩ ችግሮች፣ በተለይም ኢሰመጉ በምርጫው ወቅት በነበረው ጉልህ ተሳትፎ ምክንያት በደረሰበት ጫና እና በቀድሞው የሲቪክ ማኅበራት አዋጅ አፋኝ ድንጋጌዎች ምክንያት በተፈጠረበት የአቅም ውስንነት ምክንያት ኢሰመጉ በ2002 እና በ2007 ዓ.ም በተደረጉት አገር አቀፍ ምርጫዎች ላይ ቀድሞ የሚታወቅበትን ዓይነት ንቁ ተሳትፎ ለማድረግ ሳይችል ቀርቷል። ከዓመታት ቆይታ በኋላ በህዳር 2012 ተደርጎ በነበረው የሲዳማ ክልል ሕዝበ-ውሳኔ ላይ 10 ገለልተኛ ታዚቢዎችን በማሠማራት ከሌሎች የሲቪክ ማኅበረሰብ ድርጅቶች ጋር በጥምረት የታዚቢነት ሥራ ላይ ተሳትፏል።

- ሰኔ 14 ቀን 2013 ዓ.ም በተከናወነው 6ኛው አገር አቀፍ ምርጫ ላይ 515 ቋሚና ተንቀሳቃሽ ታዛቢዎችን፣ መስከረም 20 ቀን 2014 ዓ.ም በተከናወነው ምርጫ ላይ ደግሞ 141 ቋሚ እና ተንቀሳቃሽ ገለልተኛ ታዛቢዎችን አሰልጥኖ በማሠማራት በታዛቢነት ተሳትፎ አድርጓል።
- ሰኔ 24 ቀን 2018 ዓ.ም በተካሄደው ሀገር አቀፍ ምርጫ ኢሰመጉ በምርጫው ለመሳተፍ የሚያስችለውን ዝግጅት በከፍተኛ ተነሳሽነት የተዘጋጀ ሲሆን የመራጮች ትምህርት ስልጠና ለመስጠት እና ምርጫ ለመታዘብ የሚያስችለውን ፈቃድ ከምርጫ በርድአግኝቷል። ከተለያዩ አጋር አካላት ጋር በምርጫ ዙሪያ ለመስራት የሚያስችለውን በጀት ለማሰባሰብ ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ላይ እያለ በረቂቅ ደርጃ ወጥቶ በነበረው የሲቪል ማህበራት ማሻሻያ ረቂቅ አዋጅ ይዘት ከለጋሽ ድርጅቶች ጋር በምርጫ ዙሪያ ለመስራት የነበረው እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ተግዳሮት ፈጥሮበታል።

## 5. የምርጫ መታዘብ ዋና አላማ

- 7ኛው ሀገራዊ ምርጫ ፍትሀዊ፣ ነጻና ገለልተኛ መሆኑን ለማሳየት
- የትዝብት ግኝቱን መሰረት በማድረግ በሀገር አቀፍ ደረጃ የተካሄደ ምርጫ ላይ የታዩ ክፍተቶችን በማመላከት በቀጣይ ለሚደረጉ ምርጫዎች ማስተካከያ እንዲደረግ ምክረ ሀሳቦችን ለማቅረብ ነው።

## 6. የምርጫ ስራው ወሰን

የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ(ኢሰመጉ) ከምርጫ ቦርድ ያገኘውን የምርጫ ታዛቢነት እና የመራጮች ትምህርት የማስተማር ፍቃድን በመጠቀም በስድስት ክልሎች ማለትም በአማራ፣ ኦሮሚያ፣ በደቡብ ኢትዮጵያ፣ በሲዳማ፣ በሐረሪ እና በሶማሌ ክልሎች እንዲሁም በአዲስ አበባና በድሬዳዋ ከተማ መስተዳድሮች 433ቋሚ እና ተዘዋዋሪ ታዛቢዎችን አሰልጥኖ አሰማርቷል ። ኢሰመጉ ያሰማራቸውን ታዛቢዎች በመጠቀም የነበረውን የቅድመ ምርጫ፣ የድምፅ መስጫ ዕለት እና የድኅረ ምርጫ ሂደት ከአለም አቀፍ ስምምነቶችና ሀገር አቀፍ ህጎች አንጻር ታዝቧል።

## 7. የምርጫ ትዝብት ስነ-ዘዴ (Observation Methodology)

በኢትዮጵያ ሰባተኛው አጠቃላይ አገር አቀፍ ምርጫ ላይ ኢሰመጉ በስድስት ክልሎች በሁለት ከተማ መስተዳድሮች ከ 433 በላይ ታዛቢዎችን አሰማርቷል። ኢሰመጉ የምርጫ ሂደቱን ከምርጫ ቦርድ ትክክለኛ ዲሞክራሲያዊ ምርጫ ለማካሄድ ያስችላሉ ተብለው ከወጡ መመዘኛዎች እና አሠራሮች አንጻር ለመገምገም የቅድመ- ምርጫ ትዝብት፣ የአጭር-ጊዜ (የድምፅ መስጫ ዕለት) ትዝብት እና የረጅም ጊዜ ትዝብት የአሠራር ዘዴዎችን በጥቅም ላይ አውሏል። የዚህ እሳቤ መነሻ ምርጫዎች በድምጽ መስጫ ቀን ከሚያጋጥሙ የአንድ ቀን ክስተቶች ይልቅ ሶስቱንም ወቅቶች ያካተተ ሂደት ነው ከሚለው የኢሰመጉ ጠንካራ እምነት አንጻር ነው።

የሀገር ውስጥ ታዛቢዎች ምርጫን ለመታዘብ የተለያዩ የአሠራር ዘዴዎችን ተግባራዊ አድርገዋል። ኢሰመጉ በበኩሉ ሶስት ተመጋጋቢ የምርጫ ትዝብት ዘዴዎችን ማለትም፤ ቋሚ ታዛቢዎችን በተመጣጣኝ ስምሪት (Proportional Stationary Observation) ፣ አመቺነትን መሰረት ባደረገ የቋሚ ታዛቢዎች ስምሪት (Convenient observation) እና ተንቀሳቃሽ ታዛቢዎች (Mobile observation) ተጠቅሟል። ኢሰመጉ በተለያየ ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች የሚገኙ ባለሞያዎችን በመጠቀም ቅድመ ምርጫን ክትትል፣ የሰብዓዊ መብት ሁኔታ ክትትል፣ የሚዲያ ክትትል እንዲሁም ድህረ ምርጫ ክትትል በመስራት ከምርጫ ጋር የተያያዙ መረጃዎችን ማሰባሰብ ችሏል።

በዚህም መሰረት ኢሰመጉ በምርጫው እለት ከላይ የተጠቀሱትን ስነ- ዘዴዎች መሰረት በማድረግ ታዛቢዎችን በየምርጫ ጣቢያዎች ያሰማራ ሲሆን በዋናነትም አመቺነትን መሰረት ባደረገ የቋሚ ታዛቢዎችን ስምሪት ዘዴ በመከተል በአንዳንድ አካባቢዎች ተፎካካሪ ፓርቲዎች የሚገኙባቸው የምርጫ ጣቢያዎችን በመምረጥ 433 ቋሚና ተንቀሳቃሽ ታዛቢዎችን በማሰማራት ከ830 በላይ የምርጫ ጣቢያዎችን መታዘብ ተችሏል። በምርጫ ቀን ያሉ መረጃዎችን ለመሰብሰብ በታዛቢዎች የሚሞሉ 2 አይነት ቅጾችን ማለትም የመራጮች የድምጽ መስጫ ቀን መታዘቢያ ቅጽ እና የአሳሳቢ ኹነቶች መከታተያ ቅጽ በማዘጋጀት የምርጫ እለት መረጃዎችን ለማሰባሰብ ችሏል።

በምርጫው እለትም ቋሚ እና ተንቀሳቃሽ የምርጫ ታዛቢዎችን በማሰማራት ያበለፀገውን የመረጃ መለዋወጫ ስልት በመጠቀም በዋናው መስሪያ ቤት የኹነቶች ክትትል ክፍል በማቋቋም 25 የኹነቶች ክትትል ባለሞያወችን አሰልጥኖ በማሰማረት መረጃዎችን ከምርጫ ታዛቢዎች በቀጥታ የማሰባሰብ እና የመሰነድ ስነ ዘዴን የተከተለ ሲሆን ይህም መግለጫ ኢሰመጉ ያሰማራቸው ታዛቢዎች ለኹነት መከታተያ ክፍሉ የቀረቡን ቅሬታ፣ አቤቱታ እንዲሁም ሁሉም ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች ከታዛቢዎች የደረሳቸውን መረጃ መሰረት በማድረግ ከሰሩት የምርጫ ትንተና እና ከላይ የተገለፀው ዘዴ በመጠቀም የተገኘን መረጃ መሰረት በማድረግ የተዘጋጀ የምርጫ ሪፖረት ነው፡፡

## 8. ያጋጠሙ ተግዳሮቶች  እና የአሰራር ገደቦች

- ኢሰመጉ 7ኛው ሀገራዊ ምርጫ ላይ ለመሰተፍ በሚያደርገው ሂደት የገንዘብ እጥረት ዋና ተግዳሮት የነበረ ሲሆን ለዚህም ዋነኛ ምክንያት የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች አዋጅን ለማሻሻል በረቂቅ ደረጃ ይፋ የተደረገው አዋጅ ይዘት ባለበት ደረጃ ከፀደቀ አጋር አካላት በምርጫ ዙሪያ አብሮ ለመስራት የታሰበውን ስራ ያስተጓጉላል በሚል ስጋት አብሮ ለመስራት ፍቃደኛ አለመሆን፡፡ በዚህም ምክንያት ዓለም አቀፍ አጋር አካላት በምርጫው ዙሪያ ለሚሰሩ ስራዎች የታሰበውን የገንዘብ ድጋፍ ለማድረግ ፍቃደኛ ባለመሆናቸው ኢሰመጉ በታቀደው ልክ ታዛቢዎችን በስፋት ለማሰማራት ከፍተኛ የበጀት እጥረት ገጥሞታል፡፡
- ኢሰመጉ በኦሮሚያ ክልል ጅማ እና ነቀምት ከተማ ለማሰማራት መልምሎ ያሰለጠናቸው ታዛቢዎች ለምርጫው አንድ ቀን ሲቀር  እራሳቸውን ከታዛቢነት ማግለላቸው በእነዚህ አካባቢዎች ኢሰመጉ  የትዝብት ስራ ዕቅዱን እንዳይተገብር አድርጓል፡፡
- በሲዳማ ክልል በሀዋሰ ከተማ  ሸባዲኖ የምርጫ ክልል ደቤአፉ የምርጫ ጣቢያ የኢሰመጉ ታዛቢ በምርጫው ቀን ወደምርጫ ጣቢያው እንዳይገባ መከልከል፡፡

## 9. ከምርጫ ጋር የተያያዙ የህግ ድንጋጌዎች

ከነሐሴ 15, 1987 ዓ.ም ጀምሮ በስራ ላይ የዋለው የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት ከጸደቀበት ጊዜ ጀምሮ የ2018 ዓ.ም  ምርጫን ጨምሮ በኢትዮጵያ ሰባት አገር አቀፍና የክልል ምርጫዎች፣ ሁለት የአካባቢ ምርጫዎች እና ስምንት ሕዝበ ውሳኔዎች ተካሂዷል፡፡ የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 38 «ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ በቀለም፣ በዘር፣ በብሔር፣ በብሔረሰብ፣ በጾታ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ ወይም በሌላ አመለካከት ወይም በሌላ አቋም ላይ የተመሠረተ ልዩነት ሳይደረግበት የሚከተሉት መብቶች አሉት» በማለት የሁሉንም ኢትዮጵያውያን የመምረጥና የመመረጥ መብት ያረጋግጣል፡፡ ይሄው ተመሳሳይ ድንጋጌ የሁሉንም ኢትዮጵያውያን የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የሠራተኛ ማኅበራት፣ የንግድ ድርጅቶች እና

የሌሎች ቡድኖች አባል የመሆን መብትን ያረጋግጣል። ሕገ መንግሥቱ በተጨማሪም ተጠሪነቱ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሆነው ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ እንደሚቋቋም በአንቀጽ 102 ደንግጓል። በተጨማሪም ሕገ መንግሥቱ ከምርጫ ጋር የተያያዙ እና አግባብነት ያላቸውን ዋና ዋና የፖለቲካ መብቶች ይደነግጋል። በዚህም መሰረት በአዋጅ ቁጥር 1133/2011 የምርጫ ቦርድ ነጻና ገለልተኛ ሆኖ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተቋቁሟል።

አዋጅ ቁጥር 1162/2011፤ ይህ አዋጅ የኢትዮጵያ የምርጫ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ስነምግባርን በተመለከተ የወጣ አዋጅ ሲሆን ይህም አዋጅ በኢትዮጵያ የተለያዩ የምርጫ አይነቶችን፣ የምርጫ ሥርዓቱን፣ የምርጫ አሰተዳደሩ እርከኖችን፣ የምርጫ ሥነ ምግባርን ፣ የመራጩችና የዕጩዎች ምዝገባን፣ የምርጫ ቅስቀሳን፣ የቅሬታ አሰማማም ስርአቱን፣ የድምጽ አሰጣጥ እና ቆጠራ ሂደትን እንዲሁም የውጤት አገላለፅን የሚመለከቱ በርካታ ጉዳዮችን የያዙ ጠቃሚ ድንጋጌወችን አካትቷል። ከዚህ በተጨማሪ አዋጁ የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚመሠረቱባቸው፣ የሚዋሀዱባቸው፣ የሚተኩባቸው፣ የሚመዘገቡባቸውን እና የሚፈርሱበትን መንገዶች እንዲሁም የፖለቲካ ፓርቲዎችና አባላቶቻቸው ያሏቸውን መብቶችና ግዴታዎች በዝርዝር ይደነግጋል። በዚህ በተጨማሪ በአዋጁ ክፍል 5 ሥር ታዛቢ ቡድኖች ጋዜጠኞች እና በምርጫ ሂደቱ ላይ ክትትል ማደረግ የሚፈልጉ የፖለቲካ ፓርቲ ተወካዮች በምርጫው ሂደት ላይ ለመሳተፍ ሊከተሏቸው የሚገቡ ሕጎችን በግልጽ ይደነግጋል። ይህንን አዋጅ መሰረት በማድረግ የተለያዩ መመሪያዎች የወጡ ሲሆን ከነዚህም መካከል የሀገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢዎች ፈቃድ አሰጣጥ፣ አሠራር እና ስነ-ምግባር መመሪያ ቁጥር 5/2012 ዓ.ም እንዲሁም ለመራጮች ትምህርት ለሚሰጡ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች እና ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የመራጮች ትምህርት ፈቃድ አሰጣጥ እና ስነምግባር መመሪያዎች መጥተዋል።

በተጨማሪም የምርጫ ቦርድ አዋጅ ቁጥር 1162/2011ተወሰኑ ክፍሎችን በአዋጅ ቁጥር 1394/2017 ያሻሻለ እና አዳዲስ ድንጋጌዎችን አካቶ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አጸድቋል። ይህ የተሻሻለ አዋጅም የሴቶችን፣አካል ጉዳተኞችን ተሳትፎ የሚያበረታታ እና ቴክኖሎጅን ለምርጫ ሂደት መጠቀም የሚቻል መሆኑን የሚደነግጉ የህግ ማዕቀፎችን ያካተተ ነው ።ከዚህ በፊት በነበሩ የምርጫ ሂደቶች የሴቶች፣ የአካል ጉዳተኞች በምርጫ ያላቸው ተሳትፎ በቂ አይደለም የሚሉ እና ይህን ህጋዊ ድጋፍ የሚሰጥ የህግ ማዕቀፎች በምርጫ ህጎች እንዲካተቱ በምክረ ሀሳብ ደረጃ በተለያዩ አካላት ሲቀርብ የነበረ እንደመሆኑ እና የሴቶች እና የአካል ጉዳተኞች ተሳትፎ አሁንም ድረስ ውስንነት ያለበት በመሆኑ ይህ አዋጅ እነዚህን ጥያቄዎች በሂደት ይመልሳል ብሎ ኢሰመጉ ያምናል።

## 10. ቅድመ ምርጫ ክትትል (Pre-Election monitoring)

ኢሰመጉ ቅድመ ምርጫ ክትትል ከሚያደርግባቸው ምክንያቶች መካከል ማህበረሰቡ የመምረጥ እና የመመረጥ መብቱን በአግባቡ ያለምንም ጣልቃገብነት የመጠቀም ህገ-መንግስታዊ መብቱን መጠቀሙን ለመከታተልና ለመገምገም ነው

### 10.1. የመራጮች ምዝገባ

ዜጎች በብዙ አካባቢዎች በመመዝገብ በነፃነት የምርጫ ካርድ የማውጣት መብታቸውን በመጠቀም የምርጫ ጣቢያ በአካል በመገኘት እንዲሁም በዲጂታል ሲስተም ካርድ መውሰድ የቻሉ ቢሆንም በተወሰኑ አካባቢዎች ካለው አለመረጋጋት እና ግጭት ምክንያት በምርጫው ሂደት ሳይሰተፉ መቅረታቸውን እና በተወሰኑ አካባቢዎች የገዢው ፓርቲ ተወካዮች ወይም አባላት የሆኑ ሰዎች በተለያየ መደለያ እና ማስፈራሪያ ሰዎች የምርጫ ካርድ እንዲወስዱ ሲያደርጉ የነበረ መሆኑን ለመታዘብ ተችሏል፡፡ ለማሳያ ያህልም በጎንደር ከተማ ሴፈቲኔት ተጠቃሚ የሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎች የተወሰኑ ሰዎችን በመራጭነት የማስመዝገብ ግዴታ ተጥሎባቸው የነበረ መሆኑን፣ ተማሪዎችን መታወቂያ በመውሰድ መመዝገብ፣ በተለያዩ አካባቢዎች በሚገኙ የምርጫ ካርድ የወሰዱ ሰዎች ስልክ ላይ እየደወሉ ለምርጫ ቀን እንዳይቀሩ ማስፈራራት የደረሰባቸው መሆኑን እና በተወሰኑ አካባቢዎች የምርጫ ካርድ ካልወሰዱ ማዳበሪያ ማግኘት እንደማይችሉ በመንግስት አካላት በቀጥታ እና በተዘዋዋሪ ቅስቀሳ የተደረገ መሆኑን ኢሰመጉ በቅድመ ምርጫ ክትትሉ ለመታዘብ ችሏል፡፡ ይህ ድርጊት መራጮች በነፃ ፍቃዳቸው የመምረጥ መብት እንዳላቸው የሚደነግገውን ህገ-መንግስታዊ መብት የሚጥስ ተግባር ነው፡

### 10.2. የምርጫ ታዛቢዎች ምልመላ

በምርጫ ታዛቢነት ለመሳተፍ ፍቃደኛ የሆኑና መመዘኛውን የሚያሟሉ በተለያዩ የኢሰመጉ የማህበራዊ ድረገፆች ላይ ማስታወቂያ በማውጣት በኢሰመጉ የቅርንጫፍ ጽ/ቤት እንዲመዘገብ የቀረበውን ጥሪ በመቀበል 590 የሚሆኑ ታዛቢዎች ተመዝግበዋል፡፡ ለተመረጡት ታዛቢዎችም በየክልሉ በሚገኙ የተለያዩ አካባቢዎች ስልጠና ተሰጥቷቸዋል፡፡

**ኢሰመጉ ያሰማራቸው የታዛቢዎች ብዛት ዝርዝር**

| ቁ | አካባቢ | ቁጥር |
|---|---|---|
| 1 | ሲዳማ ክልል | 109 |
| 2 | አማራ ክልል | 60 |
| 3 | ኦሮሚያ ክልል | 22 |

| | | |
|---|---|---|
| 4 | ሱማሌ ክልል | 12 |
| 5 | ማዕ/ኢትዮጵያ ክልል | 32 |
| 6 | አዲስ አበባ | 44 |
| 7 | ሐረር | 54 |
| 8 | ድሬ ዳዋ | 22 |

ኢሰመጉ ካሰማራቸው የምርጫ ታዛቢዎች በተጨማሪ በምርጫዉ እለት የኹነቶች መከታተያ ክፍል በዋናው ቢሮ በማቋቋም 25 የምርጫ ኹነት የሚከታተሉ ባለሞያዎችን በማሰልጠን የምርጫን እለት ኹነቶች ክትትል ማድረግ ችሏል።



**የኹነቶች መከታተያ ክፍል**

## 10.3. የምርጫ ትምህርት

አንድን ምርጫ ነጻ፣ ትክክለኛ እና ተዓማኒ ለማድረግ የመራጮች ትርጉም ያለው ተሳትፎ ዋነኛው ነው። ይህንንም ለማድረግ የሚያስችላቸውን የምርጫ ትምህርት በመስጠት ዜጎች ሥነ ዜጋዊ ዕውቀት፣ ክህሎት እና ባሕሪያት እንዲያዳብሩ እና ስለ ምርጫና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ዕወቀት እና መረጃ ማስጨበጥ አስፈላጊ ነው። የኢሰመጉ የምርጫ ትምህርቶችም ዜጎች የምርጫ ሕግጋቱን ምንነት እንዲረዱ፣ በምርጫ ወቅት የሚነሡ ግጭቶች ወይም አለመግባባቶች የሚፈቱ የዳኝነት አካላት እና ሥርዓቶች መኖራቸውንና አሠራራቸውን ለማሳወቅ፣ ዜጎች በመራጭነትም ሆነ ከመራጭነት ባሻገር የሚኖራቸውን ሚና እንዲረዱ ለማስቻል፣ ለምርጫ ተነሳሽነት

እንዲኖራቸው እንዲሁም በዕውቀት ላይ የተመሠረት ምርጫ እንዲያከናውኑ በማሰብ ትምህርት ተሰጥቷል።

ለዚህም ተግባር ኢሰመጉ ከተለያዩ አጋር ድርጅቶች ጋር በመተባበር በሐዋሳ፣ ባህር ዳር፣ እና ጎንደር ከተሞች ለሚገኙ 192 በጎ ፈቃደኞች የአሰልጣኞች ስልጠና (ToT) ሰጥቷል። እነዚህ አሰልጣኞች ወደ ማህበረሰቡ በመውረድ ባደረጉት እንቅስቃሴ የሚከተሉት አበይት ክንውኖች ተመዝግበዋል፡

- **በደቡብ ኢትዮጵያ እና ሲዳማ ክልሎች፡-** በሐዋሳ፣ ሽበዲኖ፣ መልጋ፣ ጎርቼ፣ ወንዶ ገነት እና በርቻ ከተሞችና አካባቢዎች ለሚገኙ **2,694** ዜጎች ቀጥተኛ የምርጫ ትምህርት የተሰጠ ሲሆን፤ በራሪ ወረቀቶችን በማሰራጨት ደግሞ **53,880** ዜጎችን በተዘዋዋሪ ተደራሽ ማድረግ ተችሏል።
- **በአማራ ክልል፡-** በባህር ዳር እና ጎንደር ከተሞችና አካባቢዎቻቸው ስልጠናውን በወሰዱ ወጣቶች አማካኝነት **20,000** ለሚሆኑ ዜጎች ቀጥተኛ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት ተሰጥቷል። በተመሳሳይ በራሪ ወረቀቶችን በመጠቀም **250,000** ለሚሆኑ ዜጎች በተዘዋዋሪ መረጃው እንዲደርስ ተደርጓል።

በአጠቃላይ በዚህ የመራጮች ትምህርት መርሃ-ግብር **22,694** ዜጎችን በቀጥታ ፊት-ለፊት በማስተማር፣ እንዲሁም **303,880** ዜጎችን በበራሪ ወረቀቶች አማካኝነት በተዘዋዋሪ በማዳረስ የዜጎችን የምርጫ ተነሳሽነት ማሳደግ ተችሏል።



**የምርጫ ትምህርት ሲሰጡ እና በራሪ ወረቀቶች ሲያሰራጩ የሚያሳያ ምስል**



**የምርጫ ትምህርት ለመስጠት የሰለጠኑ አሰልጣኞች**

## 10.4. የዕጩዎች ምዝገባ

የዕጩነት ምዝገባን በተመለከተ በአዋጅ ቁጥር 1162/2011 በአንቀጽ31 ማንኛውም ኢትዮጵያዊ እድሜው 21 አመት ከሆነውና ከምርጫ እለት አስቀድሞ በምርጫ ክልሉ ውስጥ በመደበኛነት አንድ አመት ከኖረ ወይም የትውልድ ቦታው በእጩነት ሊቀርብበት በፈለገበት የምርጫ ክልል ውስጥ ከሆነ ወይም በእጩነት በሚወዳደርበት አካባቢ ሁለት አመት በመደበኛነት የሰራ ከሆነ እና የእጩነት መብቱ በህግ ያልተገደበ ከሆነ በእጩነት መወዳደር እንደሚችል ይደነግጋል።

በ7ኛው ሀገራዊ ምርጫ የዕጩዎች ምዝገባ በተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 1394/2017 ላይ በተቀመጠው መሰረት ማለትም የምርጫ ሂደትን ለማሳለጥና ለማዘመን እንዲረዳ በዲጂታል የዕጩዎች ምዝገባ ሲስተም መጠቀም እንደሚቻል በተደነገገው መሰረት የምርጫ ቦርድ ይህንን ወደተግባር የሚያስገባ ሲስተም በማበልጸግ እጩዎች በኦንላይን የሚመዘገቡበትን አሰራር ዘርግቷል።

ምንም እንኳ አብዛኛዎቹ ዕጩዎች በዚህ ሥርዓት መመዝገብ የቻሉ ቢሆንም፣ ሥርዓቱ የዜጎችን በፖለቲካ የመሳተፍ መብት የሚያጠብ መሆኑን በመቃወም ስምንት የፖለቲካ ፓርቲዎች በጥምረት ጥር 15 ቀን 2018 ዓ.ም መግለጫ አውጥተዋል። ፓርቲዎቹ በቅሬታነት ካነሷቸው ዋና ዋና የአሰራርና የመብት ተግዳሮቶች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡

- **የአካል ጉዳተኞችን አሳታፊነት የሚጻረር ጫና፦** አካል ጉዳተኛ ዕጩዎች ጉዳታቸውን ለማረጋገጥ ከሁለት የተለያዩ ሆስፒታሎች የህክምና ማስረጃ እንዲያቀርቡ መጠየቁ፤
- **ጥብቅ የአስተዳደር መመዘኛዎች፦** የዲጂታል ሥርዓቱን ብቸኛ አስገዳጅ አማራጭ ማድረግ እና የልደት ሰርተፊኬት ማቅረብን ለሁሉም ተመዝጋቢዎች አስገዳጅ ማድረግ፤
- **የቴክኒክ ማነቆዎች፦** ለምዝገባ የሚላከው ሚስጥራዊ የይለፍ ቁጥር (OTP) የጊዜ ቆይታ እጅግ አጭር (3 ደቂቃ) መሆን፤
- **የፓርቲ ውክልና ደንብ ጥሰት፦** ዕጩዎች ከፓርቲያቸው ዕውቅና ውጪ ራሳቸውን ከዕጩነት ማግለል የሚችሉበት አሰራር መኖሩ፣ እንዲሁም የክልል ምክር ቤት የመቀመጫ ወንበር ቁጥር ከተወዳዳሪ ፓርቲዎች ዕውቅና ውጪ መጨመሩ።

ኢሰመጉ ከነዚህ ቅሬታዎች እና ከምርጫ ቦርድ ምላሽ አንጻር የዕጩዎችን ምዝገባ ሂደት ሲከታተል የቆየ ሲሆን፣ በግኝቱም የዲጂታል ምዝገባ ሥርዓቱ አተገባበር ፓርቲዎች እና ዕጩዎቻቸው ያለምንም ማነቆ የመመረጥ መብታቸውን (Right to be Elected) ተግባራዊ ለማድረግ ከፍተኛ ተግዳሮት እንደፈጠረባቸው ለመረዳት ችሏል፡

## 10.5. የፖለቲካ ፓርቲዎች ዝግጅት እና የምርጫ ቅስቀሳ

በአዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀፅ 43(1) አንድ እጩ ተወዳዳሪ ተመዝግቦ የመታወቂያ ካርድ ካገኘበት ቀን አንስቶ ምርጫ አራት ቀን እስኪቀረው ድረስ ከአስተዳደርም ሆነ ከመዘጋጃ ቤት ፍቃድ መጠየቅ ሳያስፈልገው ፣በፁሁፍ በማሳወቅ ብቻ እና ህጋዊ ግዴታዎችን በማክበር በራሱም ሆነ በደጋፊዎቹ አማካኝነት የድጋፍ ስብሰባዎችን የመጥርት ወይም ሰላማዊ ሰለፍ የማድረግ መብት አለው በማለት ይደነግጋል።

በ7ኛው ሀገራዊ ምርጫ ከ42 በላይ የፖለቲካ ፓርቲዎች እና ብዛት ያላቸው የግል ተወዳዳሪዎች ተሳትፈዋል። እነዚህ እጩ የፖለቲካ ፓርቲዎች እና የግል እጩ ተወዳዳሪዎች ከሚጠበቁ ባቸው ተግባራት መካከል ከላይ በአዋጅ እንደተገለጸው እና እንደ ፓርቲ ጥንካሪያቸውም ከሚለካበት ተግባር መካከል ማኒፌስቶቸውን እና የፖሊሲ አማራጮችን ለመራጩ ህዝብ ማስተዋወቅ መቻላቸው ነው። የምርጫ ቅስቀሳ በተለይም የምርጫውን መቃረብ ተከትሏ በተወሰኑ ፓርቲዎች በተለይ በገዥው ፓርቲ ሰላማዊ ሰልፍ በተለያዩ ከተሞች በመጥራት ሲካሄድ ነበረ ቢሆንም ነገር ግን አብዛኛው ተፎካካሪ ፓርቲ በመገናኛ ብዙኃን ማለትም ራድዮ፣ ቴሌቪዥን በኮታ በተደለደለላቸው ጊዜ የፓርቲያቸውን ማኒፌስቶ እና ፖሊሲ አማራጫ እንዲሁም አንድ ፓርቲ በማህበራዊ ሚዲያ የተለያዩ ይዘቶችን በመጠቀም ያሉትን የፖሊሲ አማራጫ ለማቅረብ ሲይደርግ ከነበረው እንቅስቃሴ ውጭ ሰላማዊ ሰልፍ በማድረግ፣የድጋፍ ስብሰባዎችን በመጥራት የተደረገ ጥረት በቂ ያልነበረ እና ለመርጩ ማህበረሰብ በበቂ ሁኔታ እራሱቸውን እና ያሏቸውን የፖሊሲ አማራጮች በተገቢው ሳያስተዋዉቅ ወደ ምራጫ እንደገባ ኢሰመጉ ለመታዘብ ችሏል። በተወሰኑ አካባቢዎችም በሀገራችን ከለው የጸጥታ ችግር ጋር ተያይዞ ፓርቲዎች በነጻነት ከቦታ ቦታ ተንቀሳቅሰው ያላቸውን የፖሊሲ አማርጭ ለመራጩ ህዝብ ለማድረስ ተግዳሮት ፍጥሮ ባቸው እንደ ነበር እና ግጭት በነበራባቸው አካባቢዎችም የምርጫ ቅስቀሳ መድረግ በራሱ በአካባቢው ታጥቀው በሚንቀሳቀሱ ብድኖች ለጥቃት ይገልጥ የነበረ እና የምርጫ ቅስቀሳ ለማድረግ ምቹ ያልነበሩ መሆኑን ኢሰመጉ ካደረገው ቅድመ ምርጫ ትዝብት ለመገንዘብ ችሏል።

## 10.6. የሚዲያ ሽፋን

የሚዲያ ሽፋንን በተመለከተ በአዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 44 ላይ የመገናኛ ብዙኃን አጠቃቀምን በተመለከተ በመንግስት ቁጥጥር ስር ያሉትን መገናኛ ብዙኃንን ማለትም ራድዮ፣ ቴሌቪዥን እና ጋዜጦችን ተወዳዳሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች ያለ አድልዎ የመጠቀም መብት እንዳላቸው እና አጠቃቀሙን እና የምርጫ አዘጋገብን በተመለከተ የምርጫ ቦርድ መመሪያ እንደሚያወጣና በዚህም መሰረት የፖለቲካ ፓርቲዎችን የመገናኛ ብዙኃን አጠቃቀም ከብሮድካስቲንግ ባለስልጣን ጋር በመሆን በመመሪያው መሰረት የሚዲያ አጠቃቀም ድልድሉን ያከናውናል ሲል ይደነግጋል። በዚህም መሰረት የምርጫ ቦርድ የግል እጩዎችን የአየር ሰዓት ድልድል ያደረገ ሲሆን ለወንድ የግል እጩዎች 15 ደቂቃ ርዝማኔ ያለው አንድ የሬድዮ፣ አንድ

የቴሌቪዥን እና አንድ የጋዜጣ አምድ እንዲሁም ለሴት የግል ዕጩዎች ከሦስቱ የመገናኛ ብዙኃን የስርጭት አማራጮች በመረጠችው የሥርጭት አማራጭ እንድታስተላልፍ አንድ እድል ሰጥቷል፡፡

በሌላ በኩል ለወንድ አካል ጉዳተኛ ዕጩ ከሆነ በሦስት የሥርጭት አማራጮች ለአንድ ጊዜ የነበረው ነጻ የአየር ሰዓት ድልድል በመረጠው  የስርጭት አማራጭ አንድ ተጨማሪ እድል ይሰጠዋል በተመሳሳይ ሴት የአካል ጉዳተኛ እጩ ከሆነች ምርጫው ወደ አምስት ከፍ እንደሚል ቦርዱ አስቀምጧል፡፡ የመገናኛ ብዙኃንና የጋዜጠኞች የምርጫ አዘጋገብ ሥነ- ምግባር እና አሰራር መመሪያ ቁጥር 02/2013 ላይ ሁሉም የመንግስት ሚዲያዎች ለሁሉም ተወዳዳሪ ፓርቲዎች አቋማቸውን ለመራጭ ህዝቡ ለማቅረብ ፍትኃዊ እድል እንዲያገኙ የሚደነግግ ቢሆንም በ7ኛው ሀገራዊ ምርጫ ላይ ፓርቲዎች በተለያዩ የመንግስት ሚዲያዎች አቋማቸውን፣ ፖሊሲዎቻቸን ለማስተዋወቅ የተሰጣቸው የአየር ሰዓት ለገዢው ፓርቲ ከተሰጠው የአየር ሰዓት አንጻር ፍትሀዊ አለመሆኑን  እና የገዢው ፓርቲ የተሰጠውን የአየር ሰዓት የተከናወኑ የልማት ስራዎች በማሳየት የተጠቀመው ሲሆን ይህም ማህበረሰቡ ገዢውን ፓርቲ እንዲመርጥ ለማነሳሳት ተግባር ላይ መዋሉን  ኢሰመጉ ባደረገው የሚዲያ ክትትል ለማወቅ ችሏል፡፡

## 10.7. የሴቶች፣ የወጣቶች እና የአካል ጉዳተኞች ተሳትፎ

የምርጫ ሒደትን ሙሉ ከሚያደርጉት መካከል በምርጫው ሙሉ የማህበረሰብ ክፍል ነጻና ገለልተኛ በሆነ መንገድ በምርጫው ላይ ተሳትፎ ማድረግ መቻሉ ነው ይህ ሁኔታ አመላካች ከሆኑ ጉዳዮች መካከል የምርጫ ቦርድ ተጋላጭ የማህበረሰብ ክፍሎች ሴቶች እና አካል ጉዳተኞች አካታች እንዲሆን የሚያደርገው እንቅስቃሴ እና የሚወስዳቸው እርምጃዎች ዋና ማሳያዎች ናቸው፡፡ ከዚህም አንጻር የምርጫ ቦርድ አዋጅ ቁጥር 1162/2011ዓ.ም በማሻሻል በአዋጅ ቁጥር 1394/2017 ላይ የሴቶች እና የአካል ጉዳተኞችን ተሳትፎ እውቅና ሰጥቷል፡፡ ከዚህም አንጻር በእጩነት፣ በመራጭነት እና በምርጫ አስፈጻሚነት ሴቶች፣ አካል ጉዳተኞች እና ወጣቶች እንዲሳተፉ ተደርጓል፡፡ ኢሰመጉ ክትትል ባደረገባቸው የምርጫ ጣቢያዎች

- ከ50% በላይ ሴቶችና ወጣቶች በምርጫ አስፈጻሚነት የተሳተፉ መሆኑን፡፡
- የምርጫ ጣቢያዎችን የቦታ ልየታ የተደረገበት ሁኔታ ኢሰመጉ ባደረገው ክትትል በብዛት ለአካል ጉዳተኞች ምቹ የነበረ በመሆኑ በመራጭነት ለመሳተፍ ምቹ የነበረ መሆኑን ኢሰመጉ ለመታዘብ ችሏል፡፡

በእጩነት ሴቶችና አካል ጉዳተኞች የነበራቸው ተሳትፎ ውስን የነበረና ከፍተኛ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች ሊሰሩ እንደሚገባና አንዳንድ እንቅፋት የሆኑ አሰራሮች ለምሳሌ ያህል አካል ጉዳተኞች የአካል ጉዳተኝነትን ማስረጃዎች እንዲያቀርቡ የሚጠየቅበት አሰራር ቀላልና የአካል ጉዳተኞችን ተሳትፎ ሊያበረታታ የሚገባው መሆን ይኖርበታል፡፡

## ၁၁. የምርጫ ቀን ምልከታ (Election Day Observation)

### 11.1. የምርጫ ጣቢያዎች መከፈት

ኢሰመጉ ታዛቢዎችን ባሰማራባቸው የምርጫ ጣቢያዎች አብዛኛው በሚያስብል ደረጃ የምርጫ ጣቢያዎች በተያዘላቸው ሰዓት ለመራጮች ክፍት በመሆን የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱ ጊዜውን ጠብቆ የጀመረ ሲሆን የምርጫ ጣቢያዎች በየአካባቢዎቹ በቅርብ እርቀት የተቋቋሙ በመሆኑ መራጩ ማህበረሰብ እርቀት መጓዝ ሳይጠበቅባቸው በአካባቢያቸው መምረጥ መቻላቸውን እና ተጋላጭ የማህበረሰብ ክፍሎች በምርጫ ሂደቱ ቅድሚያ የተሰጣቸው መሆኑን እንዲሁም የምርጫ ጣቢያዎቹ ለአካል ጉዳተኞች ምቹ የነበሩ መሆኑን ኢሰመጉ ለመታዘብ ችሏል፡፡

### 11.2. የድምፅ አሰጣጥ ሚስጢራዊነት በተመለከተ-

ምርጫ ነፃ የነበረ መሆኑ ከሚገለፅባቸው ኹነቶች መካከል አንዱ በምርጫው እለት መራጮች በነፃነት ሚስጥራዊነቱ በተጠበቀ የምርጫ ሂደት ደምፃቸውን መስጠት መቻላቸው ነው፡፡ የተወሰኑ የምርጫ ጣቢያዎች ላይ እገዛ ለሚያስፈልጋቸው የማህበረሰብ ክፍሎች የተመደቡ ሰዎች ሳይጠየቁ ወደ ሚስጥራዊ ስፍራ አብሮ በመግባት መራጮች በነፃነት የመምረጥ መብታቸውን እንዳይጠቀሙ ተገቢ ያልሆነ እንቅስቃሴ ያደረጉ የምርጫ አስፈፃሚዎች እንደነበሩ ኢሰመጉ ለመታዘብ ችሏል፡፡ ለማሳያ ያህልም በሲዳማ የምርጫ ክልል በሀዋሰ አካባቢ በሚገኙ የምርጫ ጣቢያዎች ከሚስጥራዊ የድምጽ መስጫ ስፍራ ያለ መራጮች ፈቃድ ከመራጮች ጋር አብሮ መግባት፤ በአማራ ክልል የተወሰኑ የምርጫ ጣቢያዎች ያልተጠቀሙባቸውን የድምጽ መስጫ ወረቀቶችን ምልክት እያደረጉ ወደ ምርጫ ሳጥን ማስገባታቸውን ኢሰመጉ ለመታዘብ ችሏል፡፡



**የምርጫ አስፈፃሚዎች ከመራጩ ፍቃድ ውጭ በሚስጥራዊ ቦታ ላይ መገኘታቸውን የሚያሳይ ምስል**

### 11.3. የፓርቲ ወኪሎችና ታዛቢዎች መገኘት፤

የምርጫውን ነፃና ገለልተኝነት ማስጠበቅ ይችል ዘንድ በምርጫ ጣቢያዎች የምርጫ ታዛቢዎችና የፓርቲ ወኪሎች መገኘት ያለባቸው ቢሆንም በአንዳንድ ምርጫ ጣቢያዎች ግን የምርጫ

ታዛቢዎች እና የፓርቲ ተወካዮች በተለይ የተፎካካሪ ፓርቲ ወኪሎች አለመኖራቸውን እና ይህ ደግሞ በምርጫው ሂደት ላይ ከፍተኛ ተግዳሮት የፈጠረ መሆኑን እና በተለይም በአማራ ክልል ከከተማ ውጪ በነበሩ የምርጫ ጣቢያዎች የተፎካካሪ ፓርቲ ተወካዮችም ሆኑ ታዛቢዎች ያልተገኙ መሆኑን ኢሰመጉ ለማወቅ ችሏል፡፡

## 11.4. ጸጥታና ደህንነት

ኢሰመጉ በሀገራችን የተወሰኑ ክፍሎች ካለው አለመረጋጋት እና ግጭት ጋር ተያይዞ ለ7ኛው ሀገራዊ ምርጫ ያለውን ተጽዕኖ በቅድመ ክትትል ስራው እንዲሁም በሳምንታዊ የሰብዓዊ መብት ኹነት ክትትል ስራው ሲከታተል ቆይቷል፡፡ በትግራይ ክልል ለሁለተኛ ጊዜ በአካባቢው ሰላምና መረጋጋትባለመኖሩ ምክንያት በክልሉ ምርጫ በታቀደው መሰረት እንዳይካሄድ ሆኗል፡፡ በተለይ በአማራ እና በኦሮሚያ የተወሰኑ ክፍሎች የተለያዩ የታጠቁ ኃይሎች ማህበረሰቡን በከፍተኛ ሁኔታ በምርጫዉ ላይ እንዳይሳተፉ ማስፈራራት እና ዛቻ ሲፈፀም የነበረ መሆኑን እና ከዚህም ጋር ተያይዞ በተወሰኑ አካባቢዎች ምርጫ እንዳይካሄድ የምርጫ ቦርድ ወስኗል ፡፡ በዚህም ምክንያት የፖለቲካ ፓርቲዎች የትጥቅ ግጭት ባለባቸው አካባቢዎች ከቦታ ቦታ በነጻነት ተንቀሳቅሰው የፓርቲያቸውን ፖሊሲዎች እና ማኒፌስቷቸውን ለማስተዋወቅ ሳይችሉ ቀርተዋል፡፡ በምርጫው እለትም በ143 የምርጫ ጣቢያዎች የምርጫ ሂደቱ ተቋረጦ የነበረ ሲሆን የተወሰኑት ጣቢያዎች ለምሳሌ በአማራ ክልል በ19 የምርጫ ጣቢያዎች ተቋርጦ የነበረ ሲሆን የ15ቱ የምርጫ ጣቢያዎች ደህንነቱን በማስጠበቅ ወደነበረበት መመለስ በመቻሉ የምርጫው ሂደት መቀጠሉን እና በኦሮምያ ክልል ባሉ ቢሎኖጳ፣ መኮሳቺ ቀርሳ ምርጫ ክልሎች የጸጥታ መደፍረስ ተከስቶ የነበረ ሲሆን የጸጥታው ሁኔታ መሻሻል ባለመቻሉ ቢሎኖጳ የምርጫ ክልል ለ ግንቦት 25/2018ዓ.ም ተላልፎ የነበረ መሆኑን እና በመኮሳቺ የተፈጠረው የጸጥታ ችግር መሻሻል ባለማሳየቱ ምርጫው መቋረጡን ኢሰመጉ ለመታዘብ ችሏል፡፡

## 11.5. በምርጫ ዕለት ግኝቶች

የምርጫ ጣቢያዎች ዝግጅት ለምርጫው ሂደት ጉልህ ሚና ያላቸው እንደመሆኑ ኢሰመጉ የምርጫ ጣቢያዎች የተቋቋሙበትን ስፍራ፣ በምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ ሊገኙ እና ሊሟሉ የሚገባቸውን ፣ በምርጫ ቦርድም ሊቀርቡ የሚገባቸው እና ለምርጫው መሳካት መሰረታዊ የሆኑ ቁሳቁሶች መሟላታቸውን ከአዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንጻር ለመታዘብ ችሏል፡፡ በዚህም መሰረት ግኝቶችን እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

| ተ.ቁ | በምርጫ ጣቢያዎች የነበሩ ግኝቶች | ምን ያህል ምርጫ ጣቢያ | ምርመራ |
|---|---|---|---|
| 1 | ምርጫ ጣቢያዎች ሊቋቋሙ | በ23 | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ከሚገባቸው በታዎች ውጪ ማለትም ወታደራዊ፣ፖሊስ፣ ሃይማኖት፣ ፓርቲ ህንጻ) የተቋቋሙ | | |
| 2 | የኢሰመጉ ታዛቢዎች እንዳይገቡና የምርጫውን ሂደት እንዳይከታተሉ መከልከል | በ20 | |
| 3 | የድምጽ መስጫ ወረቀቶች ያልተሟሉባቸው ጣቢያዎች | በ 14 | |
| 4 | የመራጮች መዝገብ አለመኖሩን | በ7 | |
| 5 | የቦርዱ ህጋዊ ማህተም ጣቢያው ላይ አለመኖር | በ3 | |
| 6 | ህጋዊ የድምጽ መስጫ ሳጥኖች አለሟላት | በ13 | |
| 7 | የማይለቅ የጣት ቀለም ጣቢያው ላይ አለመኖር | በ3 | |
| 8 | ሳጥኖቹ ከመታሸጋቸው በፊት ባዶ መሆናቸው ያልተረጋገጠባቸው | በ6 | |
| 9 | ሳጥኖቹ ሲታሸጉ ወኪሎች፣ ታዛቢዎች እና አስፈጻሚዎች ያልተገኙባቸው | በ5 | |
| 10 | ሌሎች ታዛቢዎች (ከኢሰመጉ ውጭ) ጣቢያው ሲከፈት ያልተገኙባቸው ጣቢያዎች | በ25 | |
| 11 | የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ያልተቋቋመባቸው ጣቢያዎች | በ146 | |

ከላይ በቀረበው ሰንጠረዥ ላይ እንደሚታየው ኢሰመጉ በምርጫ ጣቢያዎች በተለይ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ሥነ-ምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011 እንዲሁም አዋጅ 1162/2011ን ካሻሻለው አዋጅ ቁጥር 1394/2017 ኢሰመጉ የትዝብት ስራውን የሰራ ሲሆን በእነዚህ አዋጆች በግልፅ እንደተቀመጠው በአንድ የምርጫ ጣቢያ ሊሟሉ ከሚገባቸው ነገሮች አንዱ በምርጫ እለት ቅሬታ ሰሚ ማቋቋም መሆኑን ይደነግጋል፡፡ ኢሰመጉ በ146 የምርጫ ጣቢያዎች የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ያልተቋቋመባቸው መሆኑን መታዘብ ችሏል፡፡

### 11.6. የምርጫ ጣቢያዎች መዘጋት እና ቆጠራ

በ7ኛው ሀገራዊ ምርጫ የምርጫ ጣቢያዎች የሚዘጉበትን ሰዓት በማራዘም ዜጎች ድምጽ እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡ የምርጫ ሰዓት ሊራዘም የሚችልበት ሁኔታ ያለ መሆኑ በአዋጅ ቁጥር

1162/2019 አንቀፅ 49 ላይ ቦርዱ የምርጫውን ነፃና ፍትሃዊነት ይበልጥ ያሰፍናል ብሎ ካመነ የድምጽ መስጫ ሰዓቱ ሊያራዝም እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ ነገር ግን የምርጫ ቦርድ ያደረገው የሰዓት ማራዘሚያ ግልጽነት የጎደለው እና ብዙ የምርጫ ጣቢያዎች የመዘገቧቸውን መራጮች አስመርጠው የጨረሱ ቢሆንም የቆጠራ ሂደታቸውን በመደበኛ ሰዓታቸው ማድረግ እንደሚችሉ ባወጣው መግለጫ ላይ በግልጽ ባለማስቀመጡ በተለይ የምርጫ አስፈጻሚዎች እና ታዛቢዎችን ላልተገባ እንግልት የዳረገ መሆኑን ኢሰመጉ ለመታዘብ ችሏል፡፡

የምርጫው ሰዓት እስከ ሌሊቱ 6፡00 ሰዓት መራዘም ጋር ተያይዞ ቆጠራዉ የተጀመረው ከሌሊቱ 6፡00 ሰዓት በኋላ በመሆኑ የኢሰመጉ ታዛቢዎች በምርጫ ጣቢያዎች እንዲያድሩ የተገደዱበት እና በአጠቃላይ የምርጫ አስፈፃሚዎችንም ለከፍተኛ እንግልት የዳረገ መሆኑን ኢሰመጉ ለመታዘብ ችሏል፡፡ የምርጫ ሰዓት በመራዘሙ ምክንያት በ30 የምርጫ ጣቢያዎች የድምጽ ቆጠራ ለ ግንቦት 25/2018ዓ.ም የተላለፈ መሆኑን፤ በ39 የምርጫ ጣቢያዎች የድምጽ ቆጠራው ከተጀመረ በኋላ በተለያዩ ምክንያት ማለትም የምርጫ ቦርድ መደበኛውን የምርጫ ሰዓት በማራዘሙ እና መራዘሙ የተገለጸው መደበኛው የምርጫ ሰዓት ካለቀ በኋላ በመሆኑ የጀመሩትን የድምጽ ቆጠራ ለማቋረጥ የተገደዱ መሆኑን፤ በ19 የምርጫ ጣቢያዎች በድምጽ ቆጠራ ወቅት ከፓርቲ ተወካዮች ውጪ የብልጽግና ፓርቲ አባላት በቆጠራ ሂደቱ ጣልቃ መግባት እንዲሁም በሀረር የምርጫ ክልል በፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ምርጫ ጣቢያ የድምጽ መስጫ ሳጥን መጥፋቱን እና በተወሰኑ ጣቢያዎች የምርጫ አስፈጻሚዎች እና የብልጽግና ፓርቲ ተወካዮች ምልክት የተደረገባቸው የድምጽ መስጫ ወረቀቶች ወደ ድምጽ መስጫ ሳጥን ማስገባታቸውን እንዲሁም በምርጫ ጣቢያዎች የድምጽ ቆጠራው ከተጠናቀቀ በኋላ የድምጽ ውጤቱ መለጠፉን ኢሰመጉ ለመታዘብ ችሏል፡፡

## 12. የውጤት አስተዳደር (Results Management)

ኢሰመጉ ታዛቢዎችን ባሰማራባቸው የምርጫ ጣቢያዎች አብዛኞቹ በሚያስብል ደረጃ የድምጽ መስጠት ሂደቱ ከተጠናቀቀ በኋላ የድምጽ ቆጠራ ሂደቱ የተከናወነ ሲሆን የድምጽ ቆጠራ ሂደቱም በምርጫ ጣቢያዎች በርና አካባቢዎች ላይ የተለጠፈ መሆኑን ኢሰመጉ በትዝብቱ ለመረዳት ችሏል፡፡ ይህንንም ተከትሎ የድምጽ እያንዳንድ የምርጫ ጣቢያ ውጤቱን እና የድምጽ መስጫ ኮሮጆውን በማሸግ ለምርጫ ክልሉ የላከ መሆኑን፣ የድምጽ ማዳመርና አጠቃላይ ውጤት ይፋ የማድረግ ስራ በተያዘለት ጊዜ የተከናወነ ቢሆንም ከግል ዕጩዎችና ከተለያዩ ፓርቲዎች ለምርጫ ቦርድ በቀረበው አቤቱታ እና ቅሬታ ጋር ተያይዞ ቅሬታ የቀረበባቸው የምርጫ ክልሎች ውጤትን ይፋ ሳይደረግ ቆይቷል፡፡ በመጨረሻም በምርጫ ቦርድ በቅሬታው ላይ የተሰጠውን ውሳኔ ተከትሎ የምርጫ ክልሎችን ውጤት ይፋ ማድረግ የተቻለ መሆኑን ኢሰመጉ ታዝቧል፡፡ ምርጫ ቦርድ የምርጫውን ውጤት ለመግለጽ ባደረገው ዝግጅትና ሂደት በየጊዜው ሚዲያዎችን በመጋበዝ በተለያየ ጊዜ የምርጫ ውጤት ማዳመሩ የደረሰበትን ሁኔታና

አጠቃላይ ስለ ምርጫው ሂደት በየጊዜው ማብራሪያዎችን ሲሰጥ መቆየቱ የውጤቱን ሂደት ለማህበረሰቡ ግልጽ ለማድረግ ጥረት ማድረጉን ኢሰመጉ ታዝቧል፡፡

## 13. የሰብአዊ መብቶች ግምገማ (Human Rights Assessment)

እውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ማካሄድ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ፣ ለሰብዓዊ መብቶች መከበር፣ ለሕግ የበላይነት መስፈን እጅግ ወሳኝ የሆነ መሠረት የሚጥል ነው፡፡ ከዚህም አንጻር መሰረታዊ ከሆኑት የምርጫ ሂደቶች መካከል አንዱ ፓርቲዎች የፓርቲያቸውን አቋም ለማህበረሰቡ ማስተዋወቅ እና የፓርቲዎቻቸውን ፖሊሲ እና ስርዓት በማህበረሰቡ ዘንድ ማስረጽ እንደመሆኑ በ7ኛው ሀገራዊ ምርጫ ላይ ይህንን ሀሳብን በነጻነት የመግለጽ ነጻነትን ተጠቅመው ፓርቲዎች እራሳቸውን ለማስተዋወቅ ያደረጉት እንቅስቃሴ በፊት ከነበሩት ምርጫዎች ደካማ ነበረ፡፡ የመሰብሰብና የመደራጀት መብትን በተመለከተ በኢፌዴሪ ህገመንግስት አንቀጽ 31 እና በኢትዮጵያ የምርጫ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ስነምግባር አዋጅ ሰዎች አንቀጽ 43 ላይ ለሚመለከተው አካል በጽሁፍ በማሳወቅ ብቻ ሰላማዊ ሰልፍ ማድረግ እና ስብሰባዎችን መጥራት መብት እዳለው ይደነግጋል፡፡ ኢሰመጉ እነዚህን መብቶች መሰረት በማድረግ ባደረገው ክትትል በገዢው ፓርቲ በተደጋጋሚ ሲጠሩ ከነበሩ የድጋፍ ሰልፎች ውጪ በተፎካካሪ ፓርቲዎች የነበረው እንቅስቃሴ ውስን የነበረ መሆኑን ለማወቅ ችሏል፡፡ በአጠቃላይ ኢሰመጉ ከምርጫው ጋር በተያያዘ የነበሩ የሰብዓዊ መብቶች ሁኔታዎችን በቅድመ ምርጫ፣ በምርጫ እለት እና በድህረ ምርጫ ጊዜ ሲከታተል የቆየ ሲሆን እነዚህን የሰብዓዊ መብቶች ግኝቶች በመደበኛ አመታዊ መግለጫ የሚያካትት መሆኑን ይገልጻል፡፡

## 14. ዋና ዋና ግኝቶች (Key Findings)

### 14.1. አዎንታዊ ምልከታዎች

- ፖለቲካ ፓርቲዎች ለዜጎች የሚያቀርቧቸውን አማራጮች ከዚህ ቀደም በርካታ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች አማካኝነት የውይይት/ክርክር መድረክ ሲዘጋጅ የቆየ ቢሆንም ከ 1997 ምርጫ በስተቀር በተሟላ ሁኔታ ማድረግ ባለመቻሉ፤ ይህንን ኃላፊነት ለመጀመሪያ ጊዜ ማከናወኑ ለመወጣት ጥረት መደረጉ፣
- ኢሰመጉ ታዛቢዎችን ባሰማራባቸው ምርጫ ጣቢያዎች በአብዛኛው የሴት የምርጫ አስፈጻሚዎች ቁጥር ከግማሽ በላይ መሆኑን እና በሁሉም የምርጫ ጣቢያዎች በሚባል ደረጃ ሴት የምርጫ አስፈጻሚዎች መኖራቸውን ኢሰመጉ ለመታዘብ መቻላቸውን፣
- የምርጫ ጣቢያዎች በየአካባቢዎቹ በቅርብ እርቀት የተቋቋሙ በመሆኑ መራጩ ማህበረሰብ እርቀት መጓዝ ሳይጠበቅባቸው በአካባቢያቸው መምረጥ መቻላቸውን እና ተጋላጭ የማህበረሰብ ክፍሎች በምርጫ ሂደቱ ቅድሚያ የተሰጣቸው መሆኑን እንዲሁም የምርጫ ጣቢያዎቹ ለአካል ጉዳተኞች ምቹ የነበሩ መሆኑን ኢሰመጉ

ለመታዘብ ችሏል። ይህም ይበል የሚያስብልና ወደፊት ለሚደረጉት ምርጫዎች ተጠናክሮ መቀጠል ያለበት ነው፣

- ቴክኖሎጂን መጠቀም እንደ አማራጭ ማስቀመጡ ጊዜውን ያገናዘበ ፣ የምርጫ ሂደትን ቀላል እና ቀልጣፋ ከማድረግ አኳያ ሊበረታታ የሚገባው ጅማሮ ነው፣
- በአብዛኛው የምርጫ ጣቢያዎች የነበረው የምርጫ ቁሳቁስ አቅርቦት በቂ በሚባል ደረጃ ተደራሽ መሆኑ፣
- የታዛቢዎችንና የአስተባባሪዎችን ባጅ ቀደም ብሎ አዘጋጅቶ መስጠት መቻሉ እና ተጨማሪ በተፈለገበት ወቅት ዳታቸውን ከምርጫው አንድ ቀን ቀደም ብሎ ድረስ ወደ ዳታቤዝ ለማስገባት የሚያስችል ፈቃድ መሰጠቱ፣
- በአብዛኛው በሚያስብል ደረጃ ኢሰመጉ በታዘበባቸው የምርጫ ጣቢያዎች የድምጽ መስጠት ሂደቱ በተቀመጠለት ሰዓት መጀመሩ።

## 14.2. ተግዳሮቶች/ያጋጠሙ ችግሮች

- በምርጫ ጣቢያዎች አካባቢ ከምርጫ አስፈጻሚዎች፣ ታዛቢዎች፣ የፖለቲካ ፖርቲ ታዛቢዎች፣ የግል ተወዳዳሪ ታዛቢዎች እና ከቅሬታ ሰሚ አባላት ውጪ በምርጫ ጣቢያ ውስጥ ሌሎች ሰዎች ማለትም መራጮች ካልሆኑ መገኘት እንደማይችሉ በአዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀፅ 48(2) ላይ ተደንግጓል። ነገር ግን ኢሰመጉ ታዛቢዎችን ባሰማራባቸው የተወሰኑ የምርጫ ጣቢያዎች የብጽግና ፓርቲ አባላት የሆኑ ግለሰቦች በምርጫ ጣቢያው ውስጥ የነበሩ መሆኑን እና በተወሰኑ ጣቢያዎችም ከምርጫ ጣቢያው አካባቢ የነበሩ መሆኑን እና አልፎ አልፎም ወደ ምርጫ ጣቢያው እየገቡ ይወጡ እንደነበር እና መራጩ በዚህ ሁኔታ ስጋት እንዲሰማው ያደርግ እንደነበር እና የምርጫውን ነፃና ገለልተኝነትም ጥያቄ ውስጥ የሚያስገቡ እንቅስቃሴዎች በተለይ ከከተማ ውጭ በነበሩ የምርጫ ጣቢያዎች የነበሩ መሆኑን ኢሰመጉ ለመታዘብ ችሏል ።
- ምርጫ ቅስቀሳ ከምርጫው ዕለት 4 ቀናት በፊት ጀምሮ ቅስቀሳ ማድረግ እንደማይቻል በአዋጅ ቁጥር 1162/2019 አንቀፅ 43(2) በግልፅ የተደነገገ ቢሆንም የኢሰመጉ ተንቀሳቀሽ ታዛቢዎች በተለያየ ቦታ እየተዘዋወሩ የምርጫ መታዘብ ስራቸውን በሚሰሩበት ወቅት ከምርጫ ጣቢያው በተወሰነ እርቀት ላይ የምርጫ ቅስቀሳ ያደርጉ የነበረ መሆኑን ፣ <<ማንን መረጣችሁ>> እያሉ የሚጠይቁ ሰዎች እንደነበሩ እና ለመምረጥ የሚገቡትን መምረጥ ያለባቸውን ፓርቲ ምልክት በማሳየት በነፃነት እንዳይመርጡ የፓርቲ ተወካዮች በተለይም የብልጽግና ፓርቲ አባላት ተጽዕኖ ማድረሳቸውን ለመታዘብ ችሏል።
- ዲጅታል የምዝገባ እውቅና መሰጠቱ የሚበረታታ ቢሆንም በምርጫው ቀን በተለያዩ የምርጫ ጣቢያዎች በዲጅታል ስነ ስርዓት የተመዘገቡ ሰዎች የተለያየ ምክንያት እየተሰጣቸው ይመለሱ የነበረ እና መራጮችም በምዝገባዉ ሂደት ላይ ሙሉ መረጃ እና

ግንዛቤ ካለመኖር የተነሳ የምዝገባው ሂደት ሳይጨርሱ በመቅረታቸው እና የምርጫ ጣቢያ የመረጡበት ቦታ በትክክል ባለማወቅ መራጮች እንደተጉላሉ እና የተወሰኑ መራጮችም ሳይመርጡ የተመለሱ እንደነበሩ ኢሰመጉ ለመታዘብ ችሏል።

- በ7ኛው ሀገራዊ የምርጫ ሂደት ላይ ከታዩ የጎላ ተግዳሮት ፈጥረው ከነበሩ ጉዳዩች መካከል መዝገብ ላይ የመራጮችን ስም መለየት ሲሆን ይህም በጣም እረጃጅም ሰልፍ እንዲታይ እና ሰልፎችን የሚያስተባብር በለመኖሩ በመራጮች መካከል መገፋፋት ፣ ላልተገባ ጭቅጭቅ እና መሰላቸት ምክንያት መሆኑን ለመታዘብ ችሏል። ምዝገባው ይካሄድ የነበረው በዲጂታል በመሆኑ በፊደል ወይም በተራ ቁጥር ቅደም ተከተል ባለመቀመጡ እና መዝገቡ ሹሙ አንድ ሰው ብቻ የነበረ በመሆኑ መራጮች ለረጅም ሰዓት ሰልፍ ላይ እንዲቆዩ የተገደዱ መሆኑን ኢሰመጉ ለመገንዘብ ችሏል። በተወሰኑ ጣቢያዎችም ይህን ችግር ለመፍታት በሚል ከምርጫ ቦርድ የተሰጠ አቅጣጫ ነው በማለት መዝገቡን ለሁለት የከፈሉት መሆኑን፤ አዲስ አበባ እና አካባቢው የምርጫ ጣቢያዎች በጣም በተጠጋጋ እና በአንድ ቦታ ላይ ሁለት ሶስት ጣቢያዎች የነበሩ በመሆኑ ለቁጥጥር አመች ያልሆነ እና መጨናነቆች የተፈጠሩበት ሁኔታን ኢሰመጉ ታዝቧል።
- በአንዳንድ አካባቢዎች ካለው የፀጥታ ስጋት አንፃር መንገድ መዘጋቱ የምርጫውን በሰላም እንዲካሄድ አስፈላጊ ሊሆን የሚችል መሆኑ ኢሰመጉ የሚገነዘበው ቢሆንም ከተወሰኑ የተፈቀደላቸው የትራንስፖርት አማራጮች ውጭ በሁሉም አካባቢዎች የትርንስፖርት እንቅስቃሴ መቋረጡ አንዳንድ አካባቢዎች ላይ በምርጫው ሂደት ተግዳሮት የነበረ ሲሆን ለማሳያ ያህልም ከቦታ ቦታ ተንቀሳቅሰው ይታዘቡ የነበሩ የኢሰመጉ ታዘቢዎች ይህን ተግባራቸውን ለመፈጸም ተቸግረው ነበር።
- የምርጫ ሂደቱ የተጠናቀቀበት ሰዓት ከመጠን በላይ መራዘሙ በታዛቢዎችና በምርጫው አስፈጻሚዎች ላይ ከፍተኛ የአካልና የስነ-ልቦና ጫና ፈጥሯል።
- በአማራ ክልል በባህርዳ ከተማ ቀበሌ 07 በላይዘለቀ የምርጫ ጣቢያ(የምርጫ ጣቢያ መለያ ቁጥር0306301100709) እና ቀበሌ 04(የምርጫ ጣቢያ መለያ ቁጥር 0306301100403) በድምጽ መስጫ ጣያዎች ውስጥ ወይም አካባቢ ውስጥ የገዢው ፓርቲ ተወካዮች ቅስቀሳ ሲያደርጉ የነበረ መሆኑን፤
- በአማራ ክልል ባህርዳር ከተማ በዳግማዊ ሚኒሊክ ክፍለከተማ በጣበያ መለያ ቁጥር 0306301101101 የጸጥታ አካላት በድምጽ መስጫ ጣቢያ ውስጥ በመገኘት መራጮችን ሲያዋክቡ እና በአንድ ግለሰብ ላይ ድብደባ መፈጸማቸውን ኢሰመጉ ታዝቧል።

## 15. ምክረ-ሃሳቦች (Recommendations)

- **ለምርጫ ቦርድ**
  - ✓ የምርጫ ቦርድ የምርጫ አስፈጻሚዎች ምርጫን የማስፈጸም ብቃታቸውን እና ገለልተኝነታቸውን የበለጠ ለማሳደግ ሰፊ ስልጠናዎችን እንዲሰጥ፤

- ✓ የምርጫ ቦርድ ያስጀመረው የዲጂታል የምዝገባ ስርዓትን በተመለከተ ለተመራጮችና ለመራጮች በቂ ግንዛቤ እንዲሰጥ፤
- ✓ ለሚቀጥሉት ምርጫዎች የምርጫ ቦርድ ለአሰራር ምቹ በሆነ መልኩ የምርጫ መዝገብ በፊደል ወይም በቁጥር ቅደም ተከተል እንዲያስተካክል፤
- ✓ በ7ኛው ሀገራዊ ምርጫ በዋናነት ተግዳሮት የነበረው የመዝገብ ሹሙ አንድ ሰው ብቻ በመሆኑ የመራጮችን ስም ዝርዝር በመለየት ሂደት ውስጥ ከፍተኛ ጊዜ የወሰደ ነው። ይህ አሰራር የሚሻሻልበትን ሁኔታ ምርጫ ቦርድ እንዲያመቻች፣
- ✓ ምርጫ ቦርድ ቀጣዩ ምርጫ ላይ በሁሉም የምርጫ ጣቢያዎች የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ መቋቋሙን ቅድመ-ምርጫ ማረጋገጫ ሥርዓት በመዘርጋት እንዲያረጋግጥ፤
- ✓ የምርጫ ቦርድ የምርጫ ሂደቱን እንዲያስፈጽሙ በተገቢው ህጋዊ መንገድ ካሰማራቸው የምርጫ አስፈጻሚዎች ውጭ ሂደቱን በማስተባበርም ሆነ ድጋፍ በመስጠት ተሳትፎ የሚያደርጉ ህገ ወጥ አካላትን ማስቀረት የሚያስችል የምርጫ አሰራር ሒደት እንዲዘረጋ እና ተሳትፈው ሲገኙም ፈጣን የእርምት እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችለውን አደረጃጀት እንዲዘረጋ፤
- ✓ የምርጫ ቦርድ በምርጫ ወቅት የተስተዋለውን ረዥም እና አሰልቺ ሰልፍ እንዲሁም በመራጮች ብዛት እና የምርጫ ጣቢያ መዝጊያ ሰዓት የተነሳ በመራጮች ላይ የተፈጠረውን መሰላቸትና መንገላታት እንዲሁም በምርጫ አስፈጻሚዎች ላይ እየደረሰ ያለውን የስራ ጫና ለመቀነስ የሚያስችል የአንድ የምርጫ ጣቢያ የሚያስተናግዳቸው የመራጮች ብዛት የሚወስነውን የምርጫ አዋጅ ድንጋጌ እንዲያሻሽል፤
- ✓ የምርጫ ቦርድ የምርጫ አስፈጻሚዎች ገለልተኝነታቸውን በተገቢው ሁኔታ ባስጠበቀ መልኩ ምልመላ እንዲያደርግ፣

### ❖ ለመንግስት

- ✓ መንግሥት በ7ኛው ሀገራዊ ምርጫ የተገኙ ግኝቶችን ወይም ትምህርቶችን ከፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ከሲቪል ማህበራት ድርጅቶች፣ ከምርጫ ታዛቢዎች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር የድህረ ምርጫ ግምገማ በማድረግ ለሚቀጥሉት የምርጫ ጊዜያት ገለልተኝነቱን የሚያረጋግጡ ማሻሻያዎችን እንዲያደርግ፣
- ✓ መንግስት የምርጫ ታማኝነትን ለማጠናከር እና ወደፊት በሚካሄዱ ምርጫዎች ላይ የህዝብን እምነት ለማሳደግ በአገር ውስጥ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ የምርጫ ታዛቢዎች የሚሰጡትን አስተያየቶች ተግባራዊ እንዲያደርግ፣
- ✓ ከምርጫ ጋር በተያያዘ የሲቪክ ማህበረሰብ አዋጁን ለማሻሻል በረቂቅ ደረጃ የሚገኘው አዋጅ የሲቪክ ማህበራትን በምርጫ ላይ ያላቸውን ተሳትፎ የሚያጣብብ እና በዲሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ላይ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዳያደርጉ ተግዳሮት የሚሆን እንደመሆኑ ወደፊት ይህንን ረቂቅ አዋጅ በተመለከተ የሚወሰዱ እርምጃዎች እንደገና በማጤን ቀሪ ሊያደርገው ይገባል።

### ❖ ለፖለቲካ ፓርቲዎች

- ✓ የፖለቲካ ፓርቲዎች በፓርቲ አመራርነት እና በምርጫ ዕጩነት የሴቶችን፣ የወጣቶችን እና የአካል ጉዳተኞችን ተሳትፎ እንዲያሳድጉ፣
- ✓ ምርጫ ላይ መሳተፍ አለመሳተፋቸውን ቀድመው በመወሰን መራጮቻቸውን ከሚያደናግሩ አንዴ መሳተፋቸውን የሚገልጹ ሌላ ጊዜ አለመሳተፋቸውን ከሚገልጹ መራጮችን ግራ ከሚያጋቡ አካሄዶች እንዲቆጠቡ፣
- ✓ ዜጎች አማራጭ ማግኘት ይችሉ ዘንድ የተደራጀ አሰራርን በመጠቀም በቁጥር የበዙ የተወዳዳሪ ዝርዝሮችን በማስቀረት በእውነተኛ የጋራ አቋም ላይ የተመሰረቱ በቁጥር ያነሱ ነገር ግን ከፍ ያለ የተወዳዳሪነት አቋም ያላቸው ፓርቲዎችን በመመስረት እውነተኛ መድብለ ፓርቲ የሚታይበትን ሁኔታ ማህበረሰቡ ይመለከትና ከዚህም ተጠቃሚ መሆን ይችል ዘንድ የበኩሉን እንዲወጣ፣
- ✓ ዜጎች በምርጫ ሂደት ውስጥ ያላቸውን አማራጭ ለማወቅ በሚያስችላቸው መጠን የፖለቲካ ፓርቲዎች ምርጫው ከመድረሱ በፊት እራሳቸውን እና የፓርቲያቸውን ማኒፌስቶ እንዲያስተዋውቁ፣
- ✓ የፖለቲካ ፓርቲዎች በምርጫ ወቅት የነበሩ ተግዳሮቶችን ለመለየት፣ የጋራ መግባባት ለመፍጠር እና የወደፊት ምርጫዎችን ለማጠናከር ከምርጫ በኋላ በሚደረጉ ውይይቶች እና የምርጫ ማሻሻያ ሂደቶች ላይ በመሳተፍ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲወጡ፣
- ✓ የፀጥታና ደህንነት ተቋማት የዜጎችን የመምረጥ መብት ከማስጠበቅ አኳያ ሰላምና ጸጥታ መደፍረስ የሚታይባቸው አካባቢዎች ወደ ሰላም የሚመለሱበትን ሁኔታ በማመቻቸት መራጮች በምርጫ የመሳተፍ መብታቸውን እንዲያስጠብቅ፣

❖ **ለሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች**

- ✓ የሲቪል ማኅበረሰብ ደርጅቶች ዜጎች በምርጫ ዙሪያ ያላቸውን ግንዛቤ ለማዳበር ተገቢውን የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች እንዲያከናውኑ፣

❖ **ለመገናኛ ብዙኃን**

- ✓ የብዙኃን መገናኛ ለተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች እኩል እድል እንዲያገኙ በማድረግ ስለ ፖለቲካዊ እድገቶችና የምርጫ ሂደቶች ትክክለኛ፣ ሚዛናዊ እና ገለልተኛ በሆነ መልኩ ሽፋን እንዲሰጡ
- ✓ በምርጫ ወቅት ሚዛናዊ የሚዲያ ሽፋንን በማረጋገጥ የሚዲያ ነጻነትን እና ፍትሃዊ የመረጃ ተደራሽነትን እንዲያሳድግ